# ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 27(3)፣ ስለ ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 9(2) እና በተሽከርካሪ ማበረታቻ መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 15 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 3/2003 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2004" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ ቁጥር 3/2003 (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1) የመመሪያው አንቀጽ 2 (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /3/ ተተክቷል፡፡

      " 'ሚኒባስ' ማለት ከ10 (አስር) ያላነሰ እና ከ15 (አስራ አምስት) ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው"

3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

   ይህ መመሪያ ከየካቲት 20 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ**